# የማያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል፡ የአፍሪካ ቀንድ ጉባኤ ክስረት

ዋሴ "ዘብይደሩ" በለጠ

ቀደም ሲል በበኩሌ ልጠቁም ሞክሬ እንደነበረው በኢትዮጵያ ስም ሳይሆን በአፍሪካ ቀንድ ስም በዋሽንግተን ከተማ የተካሄደው ጉባኤ ክስረት እንዳጋጠመው ግልጽ ሆኗል። ቀደም ሲል በጻፍኩት የተነሳ ከጉባኤው አዘጋጆች አንዱ አቶ ነዓምን ዘለቀ ለደብተራው በጻፉት ደብዳቤ በዋሾነት ከሰውኛል። ሁሉን አቀፍ አልነበረም ያልኩትንም አስተባብለዋል። አቶ ነዓምን እንዳሉት እነ ፕሮፌሰር መስፍንም፤ ዶክተር ታዬም፤ አቶ ዲማ፤ ሌንጮና አቶ እያሱም ተጋብዘው ከነበረ ጥረቱ ነበር ማለት እችላለሁ። አሁንም ቢሆን ለምን ቀሩ የሚለው ጥያቄ መነሳቱ ባይቀርም። ደግሞም ጉባኤው የጋራ የሆነችው ሀገራችንን ጉዳይ የሚመለከት ነውና ቀደም ሲል በፃፍኩትም ሆነ ወደፊት ጥያቄዎች ቢነሱበት አቶ ነዓምንን ጨምሮ አዘጋጆቹ ቅር ሊላቸው አይገባም። ይለቅ ከእንካ ስላንቲያው የሚሻለው ጥያቄዎቹን በገንቢነት አይቶ መወያየትና የሚታረመውን ማረም ነው። የተጋረጡ አዘናጊ ደባዎችንም ተገንዝቦ መጠንቀቅ።

የተደረገውን ጉባኤ በተመለከተ በቦታው የተገኙ ብዙ ትችት አቅርበዋል። አንዳንዶቹን ለመጥቀስ፡

- ጉባኤው 95 % ኢትዮጵያውያን የተገኙበትና ስለ ኢትዮጵያ ሆኖ ሳለ ለምን አፍሪካ ቀንድ መባል አስፈለገ? ለምንስ በእንግሊዝኛ ተካሄደ?
- በርካታ እንግዶች ለምን ቀሩ?
- ዝግጅቱ ደካማ ከመሆኑ የተነሳ የሚቀርቡት ወረቀቶች በችኮላ በላይ በላዩ የቀረቡ ሲሆን መልክ ያለው ውይይት መካሄድም አልቻለም ነበር?
- አንዳንዶቹ ኮሚሽኖች ባዶ አልነበሩምን?
- የተወሰኑ ግለሰቦች ጉባኤውን ሲቆጣጠሩ አልታዩምን?
- በጉባእው የተገኙት ስብጥርና ውጥንቅጥ ለሀሳቦች መፍለቅ ሳይሆን ለማይጨበጥ ግርግር አላመቸምን?
- ወዘተ

ከአዘጋጆቹ ጋር ለመነታረክ ፍላጎት የለኝም-- ጉባኤው ልጃቸው ነውና ከእነእንትኑ ቢያፈቅሩት ቢያደንቁት የሚጠበቅ ነው። <u>ጉባኤው ግን ከጅምሩ የተዛባ ለመሆኑ በቅርቡ ከአዘጋጆቹ አንዱ የሆኑት ዶክተር አክሎግ ቢራራ ለአሜሪካ ድምጽ ራዲዮ ከሰጡት መግለጫ መረዳት ይቻላል።</u> ይህ ጉባኤ የምርጥ ምሁራን መፈንጪያ መሆኑንና ግቡም አጠያያቂ መሆኑን ክቡር ዶክተር አክሎግ ግልጽ አድርገውልናል። ዶክተሩ ምን አሉ?

1ኛ/ የኢትዮጵያም ሆነ የአፍሪካ ቀንድ የነገ ዕጣ በውጭ ሀገር በምንኖረው ምሁሮች እጅ ነው/ በእኛ የሚወሰን ነው፤
2ኛ/ እርስ በርስ መወያየት አለብን።ከመንግስትም ጋር መወያየት መቻል አለብን።

Ethiopia: Three-day US Conference spotlights Ethiopia's future
By Peter Clottey, VOA

A three-day conference that focused on good governance, peace and security as well as sustainable development in Ethiopia and the Horn of Africa ended over the weekend in Arlington, Virginia.

Aklog Birara, a senior advisor at the World Bank and an organizer of the conference, said it was a soul-searching conference, adding that Ethiopia's future and that of the Horn of Africa will largely depend on the talent pool of experts in the Diaspora.

Birara said unity and dialogue among Ethiopians could help rebuilding efforts.

"One of the areas that we tried to explore was we can't just be constant critics. How is it that we can bridge relationships in order to contribute our part at least in building durable, strong-pluralized institutions in Ethiopia? I think the fact is that we do not reach out to one another across ethnic lines. Dialogue among us, you know. And also dialogue between the opposition parties and government. We need to really accentuate the reaching out," Birara said.

በቅድሚያ ዶክተር አክሎግ ቢራራ የዓለም ባንክ ጡረታዬን እከለከላለሁ ብለው ሳይፈሩ በጉባኤው ደፍረው በስማቸው መገኘታቸው ሊመሰገን ይገባዋል። ወይስ አንዳንዶች እንዳሉት የዓለም ባንክና አሜሪካም በተዘዋዋሪ ጉባኤውን መርቀውታል? ይህን በዚሁ እንተውና ወደ ቁም ነበሩ ስንመለስ በዶክተሩ አነጋግር ሰፍሮ የሚታየው የጉባኤው መሰረታዊ ሀሳብ ሕዝብን መናቅን ያዘለ ነው። የኢትዮጵያ ክፍለ ዕጣ ወይም የነገ ዕድሏ በምሁራን እጅ ነው ይሉናል ዶክተር አክሎግ። ይህ ራሳቸውን ዶክተር፤ ፕሮፌሰር ወዘተ ብለው እየጠሩ የሚኩራሩ ምርጦች ችግር በተለይ በአሜሪካ መረን እየለቀቀ መጥቷል። አሜሪካ ታላቅና ሀያል ሀገር ነኝ ስላለ በዚያ ነዋሪ የሆኑ የኛው ምሁራንም ይኸው ትምክህት ይንጻባረቅባቸዋል። ከእኛ በላይ አዋቂ ማለቱ ይጠናባቸዋል። ለሕዝብ እናውቅልሀለን ባይም ይሆናሉ። የነገ ዕጣችሁ በእኛ እጅ ነው ፉክራም ይከተላል። የአፍሪካ ቀንዱ ጉባኤ መነሻው ይህ መሆኑን ከአዘጋጁ አፍ እነሆ ስማን/አነበብን ማለት ነው። ያውም በውጭ ሀገር ያሉ ምሁራን-- የሀገሬውንማ ማን ከቁም ነገር ቆጥሮት! ታዲያ ይህ አያሳዝንም፤ አያስተዛዝብም? በጉባኤው ተገኙ ስለተባለው ምሁራን ትችትና ዝርዝሩን እንተወው እንጂ አነጋጋሪ ነው።

የአንዳንዱ ምሁርነት የይሁንልህ መቸም ዓይነት ነው። አንዳንዱ ኢትዮጵያን ከድቶ ለጠላቶቿ ያደረ ነው። ወንድም ነአምንን ይህ መባሉ ቅር ያሰኛችዋል ብዬ እገምታለሁ -- ቢሆንም እውነቱን ተናግሮ የመሸበት ያድሯል ነው። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ለምንስ የወያኔ አፈቀላጤ የሆኑት እነ ዴቪድ ሺን ተጋብዘው በጉባኤው እንዲያቀረሹ ዕድል ተሰጣቸው?

ዕድሜ ለእኛ ነጻ ትወጣላችሁ ጉራውን ስናልፈው ደግሞ የጉባኤው ግብ ምን እንደሆነ ዶክተር አክሎግ ነገሩን ቁልጭ አድርገው ነግረውናል። ግቡ ከመንግስት ማለትም ከውያኔ ጋርም/ መውያያት መቀራረብ ነው። ይህ ነው ዕርቅና ግጭት ማስወገድ ሲባል የነበረው በርዕስም ደረጃ? የኢትዮጵያ ልጆች ከወያኔ ጋር ያለው ግጭት ይፋፋም ዘንድ ሲጥሩ ይህ ጉባኤ ደግሞ ሊያረግብ ተነሳ! ከመለስ መንጋ ጋር ግጭት መፋፋሙ ሲፈለግ ጉባኤው ከዚሁ መንግስት ጋር ውይይት/ዳያሎግ/ ይጧጧፍ ሲል መከረ። የዘወትር ሂስ አቅራቢ አንሁን አሉ ዶክተሩ። ተቃዋሚና መንግስት ይወያዩ አሉ ዶክተሩ። የጉባኤው ግብ ይህ ከነበር ጉባኤውና የኢትዮጵያ ታጋዮች? ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ ሆነዋል። ይህ ከነበረ ግቡ ታዲያ የትጥቅ ትግል አቀንቃኝ ነን ያሉት ምን ሊሰሩ ተገኙ? በጉባኤው የተደመጠው ጥሩ አስተዳደር /ጉድ ገቨርናንስ/ እንፈልጋለን ንግግር እራሱ አጠያያቂ ነው። በፖለቲካ ጥሩና መጥፎ ብሎ ገለጣ ወይም ፍረጃ አስቸጋሪና ግልብም ነው። የምንፈልገው አስተዳደር አብዮታዊ፣ ደሞክራሲያዊ፣ ሕዝባዊ፣ ካፒታሊስታዊ፣ ሶሻሊስት ወዘተ በሚል ለመፈረጅ እንነሳለን እንጂ ጥሩ መጥፎ ማለቱ ወደ ሞራል ግምገማ የሚወድቅ ነው። ጉባኤው ከስያሜው ጀምሮ፣ የግቡ መዘባረቅ፣ የተጋባዡ ውጥንቅጥ፣ የጊዜው ማነስ፣ የሀገር ወዳዶች መነጠል/አለመገኘት፣ ፍሬያማ ውይይት ሊካሄድ አለመቻሉ፣ በጉባኤው ላይ የተወሰኑ ግለሰቦች መድረክ ማጣበብ ሲታይ ችግሩ በእኔ ግምት ጉባኤውን የረባ ፍሬ አሳጥቶታል። በጉባኤው የድርጅት መሪዎች አልተገኙም የሚለውም ሌላ ንግግር ደግሞ ሁላችንንም መናቅ ነው። ዶክተር እገሌና እገሌ የድርጅት ወይም የፖለቲካ ቡድን መሪዎች አይደሉም? ወይስ በጉባኤው ሲገኙ ይህንን ማንነታችውን በቫሌት ፓርክ ያደርጉታል?

የኢትዮጵያን ዕጣ ክፍል ወሳኝ በስደት ያለው ምሁር ሳይሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ ነውና ምሁሮች አደብ ግዙ በቁልቢው ገብርኤል። ከወያኔ ጋርም መደራደር ወይም ግጭትን መፍታት/ማርገብ የሚለውን ለወያኔና ተለጣፊዎቹ ተዉለት። ወያኔን ሁሌም በሂስ መጥረብ አናቆምም- - በሂስ ብቻ ሳይሆን በጥይት ለመቁላትም እንፈልጋለን። አዘጋጆች ይቅርታ-- ጉባኤው ከንቱ ነበር። ገንዘብም በከንቱ ባከነ! ወያኔም ዕርቅ አይፈልግ! ይልቅስ ትግሉን ለማጠናከር እንጣር!

ለደብተራው አዘጋጆች-- ጽሁፌን እንዳታወጡ የተደረገውን ጫና እምቢ ብላችሁ ስላውጣችሁልኝ አሁንም በቅድሚያ አመሰግናለሁ።